ፓኖራማ ቁጥር 96

የትዝብት አድማስ

መስከረም 8 ቀን 2003 ዓም

# አዲስ ዓመት ሲለወጥ
# የኖረው ችግር ሲቀጥል

" የመከራው ደውል ደም የተበከለ
አሁንም ቀጥሏል እየተደወለ ! "

ከአንድ ተወኔት የተወሰደ ስንኝ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ2002 ወደ 2003 ዓም በመሸጋገር አዲሱን ዓመት ተቀብሎታል፡፡ ያለው በልቶ ጠጥቶ ፥ተደስቶ ተዝናንቶ ፥ የሌለው ተርቦ ፥ተጠምቶ ፥ተከፍቶና ተቆራምዶ አሳልፎታል ፡፡በመስከረም ጧት በኢትዮጵያ ሰማይ የወጣችው ፀሀይ ግን፥እንደሰው አድልዖ ፥እንደ አምባገነኖቹ መድልዖ ስለማታውቅ ለሁሉም ዘጋ ብርሃኗን እኩል ሰጥታ አልፋለች፡፡ የተፈጥሮ ህግ በመሆኑም ሕይወት እንደወትሮው ቀጥላለች ፡፡ ኢትዮጵያና ዜጎቿም መኖር ከተባለ መኖራቸውን ቀጥለዋል ፡፡ ምናልባት ይህ ክሰተት እስከ ፍፃሜ ዓለም ይቀጥል ይሆናል ፡፡ ዜጎቿ ከሁሉም በበለጠ ቅድሚያ የሚስጡት ለሀገራቸው ኅልውና ስለሆነ በአምባገነኖች የሚደርስባቸውን ግፍና በደል በሁለተኛ ደረጃ ለማስቀመጥ ይገደዳሉ ፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት፥

" ተርቦም ተጠምቶም፥ ታርዞም ተከፍቶም
የጋራ ቤታችን ኢትዮጵያችን መልካም፥
ስጋ ያልቃል እንጅ ፥ አፅማችን አይጠፋም፥
ትውልድ ያልፋል እንጅ ታሪክ አይነካም፡፡ "

የሚለውን ብሔራዊ እሴት ለማስተናገድ ሲሉ ብቻ ነው ፡፡ ለሀገራቸው መኖር ብቻ ሲሉ ዜጎች፥ አይቀበሉት ፍዳ አይከፍሉት እዳ ፥ አይችሉት መስዋዕት እየተቀበሉ ቅድሚያ ለሀገር ልውና መስጠት ተገቢና የቆየ ባኅል ነው ፡፡ በዘመናት የተፈራረቀውም ትውልድ ይህንን

እያደረገ አልፏል ፡፡ ለአለፉት አርባ ዓመታት ሊቆጠር የማይችል ትውልድ የተመተረውም ፥ ለሀገር ነፃነትና ክብር ለሕዝብ አንድነትና ብልፅግና ለዜጎች እኩልነትና ደኅንነት፥ ለዴሞክራሲ ሥርዓትና ለብሔራዊ ልዕልና ነበር ፡፡ያ ሁሉ መስዋዕት ቢከፍልም ሀገራችን በሁለንተናዊ መስፈረት ብትመዘን አሁንም ያው የመከራ ገመዷ አልተበጠሰላትም ፡፡

የሀገራችን ሁኔታ በከፋ መልኩ መባባሱን ቀጥሏል ፡፡ አሁንም የሀገራችን ዜጎች እኩልነት አልተከበረም፡፡ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት በባዕዳን ተደፍሯል ፡፡ የምዕራቡ ለም መሬትና ድንበር ለሱዳን ተሰጥቷል ፡፡ የኢትዮጵያ ሌሎች ለም መሬቶችና ማዕደናት ለባዕድ ሀገሮች መጠቀሚያና ማበልፀጊያ እንዲሆኑ ተሰጥተዋል፡፡ የሃይማኖት መሪዎች የፖለቲካ መሳሪያ ሆነዋል፡፡ ለዘመናት አብረው የኖሩ ዜጎች እንዲለያዩ ተደርገዋል ፡፡ የሕዝብ ነፃነት ደብዛው ጠፍቷል ፡፡ ዜጎች በዘራቸው ፥ በቋንቋቸውና በክልላቸው እንዲከፋፈሉ ተደርገዋል ፡፡ በዕምነታቸው ፥ በጎሊናቸው ፥ በሰብዕናቸው ፥መከላከል ምክንያት እንበለ- ፍርድ ወኅኒ ተወርውረዋል ፡፡ ቁጥሩ በትክክል የማይታወቅ የኢትዮጵያ ዜጋ በወያኔዎቹ ተጨፍጭፏል፡፡ በልዩ ልዩ ማጎሪያ ቦታዎች ያሉ ዜጎች ለኅሊና የሚያሰቅቅ ስቃይና መከራ በመቀበል ላይ ናቸው ፡፡ የዓለም ሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች ሊቆረቆሩላቸው ቀርቶ፥የት እንዳሉ እንኳን ለማወቅ አይፈልጉም ፡፡

ስለ ኢኮኖሚው ችግር፥ስለ ማኅበራዊው ቀውስ፥ስለ ሥራ እጦቱ ችግር፥ስለ ኑሮ ውድነቱ ክብደት፥ስለ ርሀቡ ስፋትና መጠን፥ለመዘርዘር አንቃጣም ፡፡መላው ዓለም ያወቀው በመሆኑ ነው ፡፡ አምራች ሊሆን የሚችለው አፍለኛው ወጣት ትውልድ በአደንዛዥ ዕፅና በአልባሌ ባኅል ሆን ተብሎ እንዲመረዝ እየተደረገ ነው ፡፡ በሙዚቃና በአስረሽ- ምችው ፥ አዳጊው ወጣት ለሀገሩ እንዳያሰብ ፥ስለ ታሪኩ እንዳይማር ፥ ስለ ሕዝቡ ሰቆቃ እንዳይቆረቆር ፥ ስለ ነገዋ ኢትዮጵያ ራዕይ እንዳይኖረው ፥ እንዳያይ ፥ እንዳያስብ እየተደረገ ነው ፡፡ ሀገረን ለማጥፋት ደግሞ ከዚህ የበለጠ ዕኩይ ተግባር ሊኖር አይችልም ፡፡ አንድ ሀገር ተተኪውን ትውልድ ማዘጋጀት ካልቻለ፥ የነገዋ ሀገር፥ዜጋ አልባ ትሆናለች፡፡ ሀገር ደግሞ ያለ ዜጋ ብቻውን ሀገር ሊሆን አይችልም ፡፡ለም መሬቶች ለባዕዳን እየተቸበቸቡ ፥ ወጣቱና የተማረው ዜጋ እየተሰደደ ፥ ሀገር ወዳዱና ተቆርቋሪው ወገን በብዛት ወኅኒ እየወረደ ፥ የሀገር ዳር-ድንበር እየተደፈረ ፥ ዜጎች እየደኸዩ እየተራቡና እየተሰቃዩ ፥ ሀገሪቷ የባዕዳን መፈንጫ እየሆነች ታዲያ ምን ሀገርና ሕዝብ አለ ለማለት ይቻላል ?የሀገራችን ሁለንተናዊው መከራና ስቃይ እንደገና በዚህ በአዲስ ዓመት መጀመሪያ ላይ ለመግለጽ አንቃጣም ፡፡ ምክንያቱም ለአለፉት 19 ዓመተ- ፍዳ ፥ ተብሎ ተብሎ ፥ ተነግሮ ተዘክሮ ፥ ተጮኾና ተጽፎ ፥የተመዘገበ ስንክሳር በመሆኑ ነው ፡፡አዲስ የምንጨምረው ጉዳይ የለንም ፡፡

በዕኛ ዕምነት ፥ አጽንዖትና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ፥ፀሀይ የሞቀውን አገር ያወቀውን ችግር በመዘርዘር ሳይሆን፥ወይም ደግሞ የችግሩን ዋና ምክንያት ለይቶ በማወቁ ላይ ሳይሆን፥ የሀገራችንን ችግሮች መፍቻ ከማወቁ ላይ ይመስለናል ። በአዲሱ ዓመት ስለ ወያኔ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት መሆኑንና የርሱን ማንነት መዘርዘሩ ፥ በኢትዮጵያ የትግል አጀንዳ ውስጥ የቅድሚያ ጉዳይ ማድረጉ የሚያበረክተው ፋይዳ ይኸን ያህል ነው ሊባል አይችልም ። ወያኔ መወገድ እንዳለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወሰነ ዓመታት አለፈዋል ። በመሆኑም ትኩረትና ርብርቦሽ ሊያገኝ የሚገባው ወያኔን እንዴት አናሰወግደው በሚለው ላይ መሆኑ ለክርክር የሚቀርብ አይደለም ። ምክንያቱም ወያኔ ካልተወገደ የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ችግሮች እንደማይወገዱ ሁሉም ዜጋ ስለሚያውቀው ነው ።

በማነኛው ዘመን የሚገኝ የአንድ ሀገር ዜጋ የራሱን ነፃነት ሊያስከብር የሚችለው እርሱ እራሱ መሆኑ የታሪክ ሀቅ ነው ። ለዚህም ነው ከእርሱ በፊት የነበረው ትውልድም ሆነ ፥ የየካቲቱ 66 አብዮታዊ ትውልድ የዜግነት ግዴታውን ለመወጣት አይከፍሉ መሥዋዕት ለመክፈል የቻለው ! <u>በዛሪይቱ ኢትዮጵያ የተንሰራፋውን የዘረኞችን አምባገነን ሥርዓት ታግሎ ለመጣል የቅድሚያ ኃላፊነቱ ፥ ግዴታውና ተጠያቂነቱ የሚያረፈው ያለማወላወል በዚህ በአሁኑ ወጣት ትውልድ ላይ መሆኑ መታወቅ አለበት ።</u> ዕርግጥ የአሁኑ ትውልድ የዜግነት ኃላፊነቱን እንዳይወጣ ለማድረግ የወያኔ መሪዎች ልዩ ልዩ ጋሬጣዎችን እያስቀመጠበት እንደሆነ ግልጽ ነው። ስለ ጠቅላላው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ነፃነትና ደኅንነት ስለ ዜጎቿም አንድነትና ጥቅም እንዳያስብና እንዳይመለከት በጎጥና በክልል ተውስካ ተበክሎ እንዲያድግ እየተደረገ ነው ። ያልተማረውን ፥ያልተገነዘብን ፥ያልተነገረውንና ያልስማውን ለምን አላወቅኸም ለማለት አስቸጋሪ ነው ቢባልም እንኳ ፥ ይህ መሰሪ የዘረኞች ፖለቲካ ሥርዓት ያመጣበትን ጭጋግ ገፍፎ በመጣል እራሱን ከዳፍንትና ከጨለምተኝነት ነፃ ማውጣት ግን ይኖርበታል ። ለነገሩማ ፥ይህንን አስመልክቶ ፥ በኅብረ-ብሄር የተደራጁት ድርጅቶች የሚገባቸውንና የሚጠበቅባቸውን ካልሰሩ ይህንን ኃላፊነት በአሁኑ ወቅት ሌላ ማን ሊሸከመው ይችላል ? በጣም የሚያሳዝነውና በእጅጉም የሚያስተዛዝበው ፥ ትላንት በኅብረ-ብሄር ድርጅቶች ውስጥ ሲታገሉ የነበሩ ግለሰቦች ዛሬ እንደ ደረቀ ቋንጣ ተጨራምተው- ተጨራምተው በየብኄራቸውና በየጎሳቸው መሰለፋቸው ነው ። ይህንን ስንታዘብ፥ ታዲያ በወጣቱ ትውልድ ምን ይፈረድበታል ? በብሔራዊ ራዕዩ ተወዳዳሪ ያልነበረውን ትውልድ ያፈራው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአሁኑ ወቅት የጎጠኞችና የጠባቦች ማዕከል መሆኑ ፥ የቱን ያህል ብሄራዊ ትራጀዲ ማየት እንደሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ የማያቋርጥ ሀዘን ሆኖበታል ። በወያኔ ዘረኛ ሥርዓት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተቋማት በዘር ቅኝት መዋቀራቸው አልበቃ ብሎ፥ የትምህርትና የሐይማኖት ተቋማትም ጭምር በክልልና በጎጥ መዋቀራቸው የነገዋን ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና

ሀገራዊ አጀንዳ ማን እንደሚያራመደው አይታወቅም ። ወያኔ ሀገሪቷን አጠፋት ሲባል እኮ ይህንንም ሁሉ በማሰብ ጭምር ነው ።

ለነገዋ ኢትዮጵያ ዛሬ የሚያስብ ትውልድ እንዳይኖር ማድረግ የወያኔዎቹ ዕቅድ ስለሆነ ይህንን የሀገር ደመኛ ቡድን ማስወገድ ይገባል የሚባለው ለዚሁ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን አዲስ ዓመት ሲቀበል፥ ሀገሩ ኢትዮጵያና ዜጎቿ የወደቀባቸውን መሪር ሀዘን፥ ብሔራዊ ጥቃት፥ ሁለንተናዊ ጥፋትና ሀገራዊ ውርደት ሁሉ በአዕምሮው እያሰላሰለ ነው።እንደ ባኅሉና እንደ ልምዱ ቢሆንማ ኖሮ፥ “ መስከረም ሲጠባ አደይ ሲፈነዳ ፥እንኳን ሰው ዘመዱን ይጠይቃል ባዳ። ” እያለ ይዘምር ነበር ። ዛሬ ፥ ያን የሚልበት የደስታ ስሜትና፥ የአዲስ ዓመት ተስፋ የለውም። አዲሱ ዘመን የሚያመጣለት አንዳችም የሕይወት ለውጥ እንደሌለ ያውቀዋል። የኑሮው ውድነት፥ የዕቀዎች ዋጋ ግሽበትና የሥራ ማጣት፤ረሀቡ ሕይወቱን መራራ አድርጎታል። የአንድ ዶሮ ዋጋ ሁለት መቶ ብር ደርሷል ከተባለ ስንቱ ደሃ ነው በዐውድ-ዓመቱ ዶሮ አርዶ አዲሱን ዓመት ሊያከብር የሚችለው? ስንቱስ ዜጋ ነው የበግ ዱለት ሊቀምስ የሚችለው ? በዘመን መለወጫ በዓል፥ ደሃ፥ ሊላው ቢቀር፥ ዶሮ አርዶ ካልተመገበ ምኑን በዓል ሆነው?

“ በቅዱስ ዮሐንስ፥ ዘመን መለወጫ ካልተገኘች ዶሮ፥
በዓል ማክበር ትቼ ቀኑን አሳልፍኩት በሀዘን ሮሮ
ችግሩን ስቃዩን ልመድልኝ ሆዴ
እንኳን የዶሮ ወጥ አልተገኘም ዶኬ። ”

ይህ እንጉርጉሮ ዛሬ በኢትዮጵያ የሚሰማው በበዓል ጊዜ ብቻ ሳይሆን ዘወትርም ነው ። እንደ ሀገራችን ባኅልና እንደ ታሪካችንማ ቢሆን ኖሮ ፥የምንታገልለትን የኢትዮጵያን ሕዝብ ቄጠማ ጎዝጉዘን፥ አበባ ቀንጠስን እንኳን ለአዲሱ ዘመን አደረሰኽ ! ማለት በተገባን ነበር። በዚህ በአዲሱ ዓመት ልንለው የምንችለው ግን ፥ከወያኔ መሪር አገዛዝ ነፃ እንድትወጣ ትግላችንን ቀጥለናል! አንተም በዘረኞች መርዝ ሳትበከል፥ አንድነትህን አጠንክረህ ወያኔን ለማስወገድ ተባበር የሚል ብሔራዊ ጥሪ ማስተላለፍ ብቻ ነው !

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረስህ !
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !
እኛም ትግላችንን እንቀጥላለን !